# የአማርኛ ትምህርት የፈተና መለማመጃ ጥያቄዎች

## ክፍል ሶስት

1. አሁንማ ሁለቱ ጓደኛሞች **ሆድና ጀርባ** ሆነዋል ሲል የተሰመረበት ቃል ፍቺ

ሀ) ቤታቸው ፊትና ኋላ ነው ለ) ተቃቅረዋል

ሐ) በጣም ይዋደዳሉ መ) ሀ እና ሐ

2. **መዳፈ ሰፊ** ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ፍቺ የሚሆነው

ሀ) እጁ ትልቅ ለ) ለጋስ ሐ) ደግ መ) ለ እና ሐ

3. ለእሱ መንገር እኮ **እየፈጩ ጥሬ** ነው ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ሀ) ልጁ አይሰማም ለ) እህሉ ሊደቅ አይችልም

ሐ) ወፍጮው በደንብ አይፈጭም መ) ሀ እና ለ

4. **ህልቆ መሳፍርት** ማለት ምን ማለት ነው ?

ሀ) በጣም ሰፊ ለ) በጣም ብዙ

ሐ) ተሰፍሮ የማያልቅ መ) ለ እና ሐ

5. **ተብረከረከ** ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ሀ) ተጨነቀ ለ) በጣም ደነገጠ

ሐ) ፍርሃት ያዘው መ) ለ እና ሐ

6. **የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ አለ ሲል ምን ማለቱ ነው ?**

ሀ) ትልቅ ጆሮ ይስጠኝ ለ) አልሰማም

ሐ) ወፍራም ጆሮ ይስጠን መ) ከባድ ጆሮ ይስጠኝ

7. አደብ ገዛ ሲል ምን ለማለት ነው

ሀ) ተረጋጋ ለ) ጥሩ ባህሪ አሳየ

ሐ) መሬት ገዛ መ) ሃ እና ለ

8. **የጅብ ፍቅር** ሲል የዚህ ፈሊጥ ፍቺ የሚሆነው

ሀ) ማታ ማታ ብቻ የሚከሰት ለ) ለከፉ ጊዜ የማይሆን

ሐ) ቀን ሲበላሽ የሚቀየር መ) ለ እና ሐ

LIVEWORKSHEETS

9. ***ግንትር ፀሀይ*** ማለት ምን ማለት ነው ?

ሀ) ለሰስ ያለ | ለ) በጣም የሚያቃጥል

ሐ) ደመና የሸፈነው | መ) የማያረከስ ፀሃይ

ጎጃምና ጎንደር ምን ያደርግልኛል

ለኔ ለኡሮዬ ባሌ ይሻለኛል፣

10. የዚህ ቅኔያዊ ግጥም ሰም ምንድን ነው ?

ሀ) የትዳር አጋሬ | ለ) ባሌ የተባለው ቦታ

ሐ) ባለቤቴ | መ) ጎጃምና ጎንደር

አደባባይ ቆሜ እያለሁ ዝም ብዬ፣

ማቅን የለበሰ አገናለሁ ብዬ፣

11. የዚህ ቂኔያዊ ግጥም ህብረ ቃል የሆነው፡

ሀ) አደባባይ ቆሜ | ለ) አገኛለሁ ብዬ

ሐ) ማቅን | መ) ዝም ብዬ

12. የቅጥያዎች ሰዋሰዋዊ አገልግሎት ምንድን ነው?

ሀ) ብዛትን መግለጽ | ለ) ጾታን መግለጽ

ሐ) ባለንብረትነትን መግለጽ | መ) ሁሉን

13. ቃላዊ ግጥሞች የኔ ባይ ባለቤት ወይም ደራሲ የሌላቸው በምን ምክንያት ነው ?

ሀ) ደራሲያቸው ስለማይታወቅ | ለ) የተጻፉበት ዘመን ስለማይታወቅ

ሐ) ህዝብ የወል ሃብት ስለሆኑ | መ) ሁሉም መልስ ናቸው

14. የከሚከተሉት አማራጮች መካከል የተገብሮ ግስ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ቀደደው | ለ) ተቀደደ | ሐ) ቀደደችው | መ) ቀደዳችሁ

15. ከሚከተሉት የሃረግ አይነቶች ስማዊ ሃረግ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) የወርቅ ቀለበትህ | ለ) ወንድሙ ከፉኛ

ሐ) ከእህቷ ጋር | መ) በጣም ቆንጆ

LIVEWORKSHEETS

16. ትምህርት ቤት መጣ ፡፡ የተሰመረበት ሃረግ አይነት ምን ይባላል?

ሀ) ስማዊ ሃረግ ለ) ግሳዊ ሃረግ ሐ) ቅጽላዊ ሃረግ መ) መስተዋድዳዊ ሃረግ

17. ፅድቁ ቀርቶ..................

ሀ) በቅጡ በኮነነኝ ለ) በደንብ ባበላሁኝ

ሐ) ፅዕሎት ባወቅሁኝ መ) ምስኪን በረዳሁኝ

18. በአንድ ድንጋይ.................

ሀ) መወራወር ለ) ሁለት ወፍ

ሐ) መጫወት አይቻልም መ) ቀልድ የለም

19. **አይነ ልም** ለሚለው ፈሊጣዊ አባባል ፍቺ የሚሆነው ፡

ሀ) ምቀኛ ለ) ቆንጆ

ሐ) ተንኮለኛ መ) የዋህ

20. ከሚከተሉት ውስጥ የምክንያትና ውጤት ንፅፅር የሚያመለክተው የልብወለድ አላባ የትኛው ነው ?

ሀ) መቼት ለ) ግጭት ሐ) ጭብጥ መ) ሴራ

21. ከሚከተሉት ውስጥ የብዛትን እና የባለንብረትን ምዕላድ አጣምሮ የያዘው የትኛው ነው ?

ሀ) ጓደኛዬ ለ) ባልደረባዬ ሐ) ወንድሜ መ) ባልደረቦቼ

22. ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት መካከል <u>**ኣማ**</u> የሚለውን አብዢ የሚወስደው የቱ ነው ?

ሀ) ብርድ ለ) ሰው ሐ) በሬ መ) ሃገር

23. ከሚከተሉት መካከል በግል አስተያየት ላይ የተመሰረተው የቱ ነው ?

ሀ) የአካባቢ ብክለት ለጤን ችግር ያስከትላል።

ለ) አልኮል ለሆድ ቁርተት መድሐኒት ሳይሆን አይቀርም

ሐ) ፀሃይ የብርሃን እና የሙቀት ምንጭ ናት

መ) ትምህርት ለአንድ ሀገር እድገት መሰረት ነው

24. ከሚከተሉት አማራጭዎች ውስጥ ጠብቆ እና ላልቶ ሲነገር የተለየ ትርጉም ሊሰጥ የሚችለው ቃል፡

ሀ) ሄደ ለ) ጻፈ ሐ) ጠላ መ) ተጫወተ

LIVEWORKSHEETS

25. ጭንቀት ለአእምሮና አካላዊ ጉዳት ይዳርጋል። በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ ለውጤቱ መስዓኤ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) አካላዊ ጉዳት ለ) የአ አምሮ መታወክ ሐ) ጭንቀት መ) ጉዳት

26. **ንግግር አያውቅም** ለሚለው አገላለጽ ትክክለኛ ፍቺ ሊሆን የሚችለው፡

ሀ) ቋንቋ አያውቅም

ለ) የመስማትና የመናገር ችሎታ የለውም

ሐ) ቃላት ሳይመርጥ አፉ እንዳመታለት ይናገራል

መ) ገና አፉን አልፈታምና ንግግር አይችልም

27. ከሚከተሉት አንዱ ከአጭር ልቦለድ ውስጥ የማይካተት ነው።

ሀ) ብዙ ገጸ ባህርያትን ያሳትፋል ለ) ነጠላ መልዕክት ያስተላልፋል

ሐ) ቅርጹ ውስን ነው መ) መቼቱ ጠባብ ነው

28. ለአንድ ነገር ወካይ በማቆም የምንገልፅበት የዘይቤ አይነት .......... ይባላል፡፡

ሀ) ግነት ለ) አያዎ

ሐ) ተለዋጭ መ) ተምሳሌት

29. ልጁ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ ፡፡ የተሰመረበት ሃረግ አይነት ምን ይባላል?

ሀ) ስማዊ ሃረግ ለ) ግሳዊ ሃረግ ሐ) ቅጽላዊ ሃረግ መ) መስተዋድዳዊ ሃረግ

30. ከሚከተሉት አንዱ የአጭር ልቦለድ ባህሪ አይደለም

ሀ) ነጠላ ውጤት ለ) ጥድፊያ

ሐ) ቁጥብነት መ) ትልም

31. የደላው..........................................

ሀ) አልጋ ላይ ይተኛል ለ) ሙቅ ያኝካል

ሐ) ማስቲካ ይበላል መ) ይጫወታል

32. አለባብሰው ቢያርሱ..................................

ሀ) በትልቁ ይጎርሱ ለ) በትንሽ ይጎርሱ

ሐ) ባረም ይመለሱ መ) ከመሬት አይነሱ

LIVEWORKSHEETS

33. ሙብላቷን ሳታውቅ.....................................

ሀ) እራባት

ለ) ምግብ ሰራች

ሐ) እጇን ታጠበች

መ) እንቅልፏን ተኛች

34. ለተቀማጭ.....................................

ሀ) ሁሉ ቀላል ነው

ለ) ሰማይ ቅርቡ ነው

ሐ) መንገድ ቀላል ነው

መ) መነሳት ከባድ ነው

35. የረጋ ወተት.....................................

ሀ) ይናጣል

ለ) ወፍራም ነው

ሐ) ቅቤ ይወጣዋል

መ) የሚንጥ ይበዛዋል

LIVEWORKSHEETS